# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ሰኔ 4 ቀን 2003 ዓ.ም**

**የኮሎኔል ተስፋዬ አሙዋሙዋት እያነጋገረ ነው ተባለ፤**

**በቃሊቲ እስር ቤት የሚገኙትን የደርግ ባለስልጣናት እየከፋፈሉ ሊፈቱዋቸው መሆኑ ተጋለጠ፤**

**የደቡብ ክልል ፕሬዝዳንት የቁም እስር ላይ መሰንበቱ ተጠቆመ**

**ህዝቡ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እየዳከረ ለጅቡቲ መብራት መስጠት ተጀመረ፤**

ለ17 ዓመት በህዝብ እና በሀገር ላይ ደባ ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ ከነበሩት ዋነኛ የደርግ ባለስልጣናት መሀከል አንዱ የነበረው ኮሎኔል ተስፋዬ ወ/ስላሴ ድንገት ሞተ መባሉ እያነጋገረ መሆኑ ታወቀ።

የመንግስቱ ኃይለማርያም ቀኝ እጅ እና ምስጢር ጠባቂ የነበረው ይሄው ግለሰብ ወያኔ ስልጣን ከያዘበት ግንቦት ወር 1983 ዓ.ም ጀምሮ ለ20 ተከታታይ ዓመታት በእስር ቤት ያሳለፈ ቢሆንም ዓርብ ግንቦት 26 ቀን 2003 ዓ.ም ከሰዓት በሁዋላ ድንገት በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ሞቶ መገኘቱን የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ።

የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው 20 ዓመታትን በእስር ላይ ያሳለፉት የደርግ ባለስልጣናት ፍርዳቸው ተሻሽሎ ወደ እድሜ ልክ እንዲቀየርላቸው ረቡዕ ግንቦት 24 ቀን 2003 ዓ.ም በይፋ በፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ በተነገረ በሁለተኛው ቀን ድንገት ሳይታሰብ በቃሊቲ እስር ቤት የህክምና መዕከል ውስጥ ሞቶ መገኘቱ እያነጋገረ ከመሆኑም በተጨማሪ በደርግ ባለስልጣናት እና በፖሊሶች መሀከል ከፍተኛ ብጥብጥ ተከስቶ እንደነበር የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ለአንድ አፍታ ወደ ህክምና ማዕከል የሄደው ኮሎኔል ተስፋዬ ወ/ስላሴ ድንገት የእረፍቱ ዜና ለባልደረቦቹ ሲነገር በመበሳጨት እና በመደናገጥ በአጠገባቸው የነበሩትን ፖሊሶች በመሳደብና በማባረር ከፍተኛ ረብሻ የፈጠሩ ከመሆኑም በተጨማሪ በጩኸት እና ቀርቀሮ በማንኩዋኩዋት ተቃውሞ ሲያሰሙ ሌሎች ክፍሎች ውስጥ ያሉ እስረኞች ድምጻቸውን በመስማት

በየክፍላቸው አረብሻ በማንሳታቸው የተነሳ ቃሊቲ እስር ቤት ዓርብ ዕለት በተቃውሞ ስትናጥ እንዳመሸች ምንጮቹ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

የወያኔን እድሜ ለማራዘም ሲባል በመለስ ትዕዛዝ ሰጪነት እና በእምነት አባት ነን ባዮቹ በአነ አባ ገብረመድህን ልመና ከሞት ፍርድ ወደ እድሜ ልክ ይቅርታ የተደረገላቸው እስረኛ የደርግ ባለስልጣናት በቀጣይ ቀናት ደግሞ ሙሉ ምህረት ሊደረግላቸውና ከእስር ሊወጡ ይችላሉ ተብሎ ቤተሰቦቻቸው በተስፋ ሲጠባበቁ ባለበት ወቅት ድንገት ተስፋዬ ሞተ መባሉ እያነጋገረ መሆኑም ታውቆዋል፡፡

ይቅርታው ከተነገራቸው ሁለት ቀናት በሁዋላ ዓርብ ዕለት ሁለት የደርግ ባለስልጣናት ብቻ ስማቸው ተጠርቶ ተነጥለው ከእስር ቤት ድንገት በምስጢር ለቃለ ምልልስ እንዲወጡ በመደረጉ የተበሳጨው ይሄው ኮሎኔል ተስፋዬ እኛ ተነጥለን ለምን እንቀራለን ምን ልዩነት አለን እያለ በብስጭት የእስር ቤቱን አዛዦች ሲናገር እንደነበርና ከዚሁ ጋር በተያያዘ አለመግባባት ተፈጥሮ ለረዥም ሰዓት ሲበሳጭ እንደነበረና ድንገት እራሴን ብሎ ወደ ህክምና ተወስዶ ጥቂት እንደቆየ መሞቱን ያጋለጡት ምንጮቹ ይህን ተከትሎ በእስር ቤት ከፍተኛ ረብሻ ተፈጥሮ እንደነበር አጋልጠዋል፡፡

እንደ ምንጮቹ ጥቆማ ከሆነ ፍስሀ ደስታ እና ደበላ ዲንሳ ድንገት ስማቸው ተጠርቶ ትፈለጋላችሁ ሙሉ ልብስ ለብሳችሁ ውጡ በመባላቸው የተደናገጡት የቀሩት እስረኞች እኛ ለምን ተነጥለን ቀረን እያሉ ሲቆጡና ሲበሳጩ እንደነበር ምንጮቹ ገልፀው በተለይ ኮሎኔል ተስፋዬ በቁጣና በንዴት እኛስ ለምን ተዘነጋን በማለት በወቅቱ እስር ቤት ከመጡ የወያኔ የእስር ቤት ሹሞች ጋር ግጭት ፈጥሮ እንደነበር አጋልጠዋል፡፡

በወቅቱ በከፍተኛ ሁኔታ ተበሳጭቶ የነበረው ኮሎኔል ተስፋዬ የወያኔ የእስር ቤት ሹሞችን እየተሳደበና እየገላመጠ እንደነበር የጠቆሙት ምንጮቹ ወዲያው እራሴን ብሎ ግቢው ውስጥ ወደሚገኘ ው ጤና ጣቢያ ቢወሰድም ከጥቂት ሰዓት ቆይታ በሁዋላ ሞተ ተብሎ በመነገሩ በእስር ቤት ያሉት የደርግ ባለስልጣናት ወያኔዎች በመርፌ ገደሉት እያሉ እያለቀሱ ግቢውን ሲያምሱት እንደተደመጡም ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

የደርግ ባለስልጣናትን ጩኸት እና ለቅሶ የሰሙ ሌሎች ዞን ውስጥ ያሉ የወያኔ የግፍ ሰለባ የሆኑ እስረኞች የነሱን ጩኸት በመድገምና በማስተጋባት አልፎ ተርፎ ቆርቆሮ በመደብደብ ከፍተኛ ተቃውሞ በማሰማታቸው የተደናገጡት የቃሊቲ እስር ቤት አለቆች በተለይ አብርሀም ወ/አረጋይ የተባለው የቃሊቲ እስር ቤት አዛዥ ለአለቆቹ ድጋፍ ሰጪ ኃይል እንዲመጣለት ጥሪ በማቅረቡ ወዲያው በሁለት ፓትሮል የተጫኑ የፌዴራል ፖሊሶች እና መትረየስ የደገኑ ፓትሮሎች ዙሪያውን መክበባቸው ገልጸዋል፡፡

በቃሊቲ እስር ቤት ዋና አዛዥ አብርሀም ወ/አረጋይ ጥሪ ተደርጎለት ወደ ግቢ ውስጥ ዘልቆ የገባው የፌዴራል ፖሊስ በበኩሉ እስረኞቹን በዱላና በመሳሪያ ሰደፍ እየደበደበ ብዙዎቹን እስረኞች ሲያሰቃያቸው እንደነበር የገለፁት የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ከነሱም መሀከል ተመርጠው ጨለማ ቤት ተብሎ በሚጠራው ክፍል ነጥለው እንዳሰሩዋቸውም ምንጮቹ አብራርተዋል፡፡

ወያኔ የስልጣን እድሜውን ሊያራዝም ዕቅድ ከያዘበት የህዳሴው ግድብ ጋር ተያይዞ በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ በሚገኙ የደርግ ባለስልጣናት መሀከል ብዙ ልዩነት ተፈጥሮ እንደነበር ያስታወሱት የዜና ምንጮቹ ደበላ ዲነሳ እና ፍስሀ ደስታ ለግድቡ የሚውል ከየኪሳቸው እያንዳንዳቸው 2ሺህ ብር የሰጡ ከመሆኑም በተጨማሪ በእስር ቤት ውስጥ በቡድን ካጠራቀሙት 80 ሺህ ብር ላይ 40 ሺህ ብሩን ለዚሁ አባይ ግድብ እንዲዋጣ በማድረጋቸውና ወያኔ የጀመረውን የልማት ስራ አድንቀው መግለጫ በመስጠታቸው የተነሳ ከሌሎች እስረኞች ጋር ቅራኔ ፈጥረው እንደነበረም ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

ኮሎኔል ተስፋዬ ወ/ስላሴ ዓርብ ግንቦት 26 ቀን 2003 ዓ.ም መሞቱ ተገልፆ እስከ ሰኞ ድረስ በዚያው በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ አስከሬኑ እንዲቆይ ተደርጎ ሰኞ ግንቦት 29 ቀን 2003 ዓ.ም ከሰዓት በሁዋላ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ተወስዶ በማግስቱ ማክሰኞ ለቤተሰቦቹ እንደተሰጠና በዚያው ዕለት በኮተቤ አቅራቢያ በሚገኘው ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን የቀብሩ ስነስርዓት እንደተፈጸመ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ባለፈው ሳምንት ከሞት ፍርድ ወደ እድሜ ልክ እንደተሻሻለላቸው በይፋ ከተነገረ በሁዋላ በእስር ላይ የሚገኙትን የደርግ ባለስልጣናት ዋልታ ኢንፎርሜሽን የተሰኘው የወያኔ ሚዲያ የሆነው ማዕከል ለሁሉም እስረኞች ቃለ ምልልስ አድርጎላቸው ለህዝብ ይተላለፋል ተብሎ ሲጠበቅ ድንገት ከጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ የመጣ ትዕዛዝ በሚል ሳይተላለፍ መቅረቱን የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ፡፡

በቃለ ምልልሱ ላይ ሙዋቹ ኮሎኔል ተስፋዬ ወ/ስላሴን ጨምሮ ሁሉም እስረኛ የደርግ ባለስልጣናት የተሳተፉበት ሲሆን በዚሁ ቃለ መልልስ ላይ የበደሉትን ህዝብ ተንበርክከው ይቅርታ ለመጠየቅ መዘጋጀታቸውን የሚያሳይ ቀረጻ ተደርጎ ሊተላለፍ በዝግጅት ላይ እንዳለ ድንገት እንዳይተላለፍ መደረጉን ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል፡፡

በዚሁ በተደረገላቸው የቃለ ምልልስ ቀረጻ ላይ ከጥቂቶቹ የደርግ ባለስልጣናት በስተቀር ሙዋቹን ተስፋዬ ወ/ስላሴን ጨምሮ ሁሉም ወያኔን ይቅርታ ሳይጠይቁ የኢትዮጵያን ህዝብ ብቻ ተንበርክከን ይቅርታ አድርግልን በማለታቸው የተቆጡት እነ መለስ ዜናዊ እንዳይተላለፍ ከማገዳቸውም በላይ እንደገና እንዲቀረፁ መታዘዙንም ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

ይህንኑ ተከትሎ ደግሞ በቅርቡ ለሁሉም ምህረት እንዲደረግላቸው የእምነት አባት ነኝ ባዮቹ ጥያቄ እያቀረቡ ባለበት ወቅት አስር ለሚሆኑት ብቻ ይቅርታ ፎርም ሞልታችሁ አቅርቡ ብሎ በረሀ አመጣሹ የቃሊቲ እስር ቤት አዛዥ አብርሀም ወ/አረጋይ እንዳዘዛቸው የገለጹት ምንጮቹ ቀሪዎቹ ፎርሙ እንዳልተሰጣቸውም ገልፀዋል፡፡ በእስረኞቹ መሀከል ልዩነት ፈጥረው ፎርም የታደላቸው በቃለ ምልልሱ ላይ እያሽቃበጡ የወያኔን ልማታዊ መሆን የመሰከሩት የደርግ ባለስልጣናት ብቻ መሆኑንም ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

ይቅርታ ፎርም ሞልታችሁ አቅርቡ የተባሉት አስሩ የደርግ ባለስልጣናት ለግዜው እነማን እንደሆኑ ባይታወቅም በእስር ቤት ውስጥ ለወያኔ ሲያጎበድዱና ሳይጠሩዋቸው አቤት ሳይልኩዋቸው ወዴት ሲሉ የነበሩት ብቻ ተመርጠው ሳይሆን እንደማይቀር ምንጮቹ ጨምረው አስረድተዋል፡፡

በሌላ ዜና ወያኔ ስልጣን የተቆናጠጠበትን ቀን ለማክበር በጠራው የአደባባይም ሆነ የአዳራሽ ስብሰባ ላይ የገዛ አባሎቹ ሳይገኙ በመቅረታቸው እርስ በርስ መወነጃጀል እና መነታረክ መጀመራቸው ታወቀ::

ቅዳሜ ግንቦት 20 ቀን 2003 ዓ.ም የወያኔ ቡድን የ20ኛ ዓመት በዓሉን ለማክበር በመስቀል አደባባይ እንዲገኙለት መኪና አቅርቦ እና ውሎ አበል ለአባሎቹ ቢከፍልም ከ75 በመቶ በላይ የሆኑት ሳይገኙ በመቅረታቸው ለከፍተኛ ባለስልጣናት ትልቅ የራስ ምታት እንደሆነባቸው ታውቆዋል::

የወያኔ ቡድን ለከፍተኛ ባለስልጣናቱና ከበረሀ ለመጡ የህወሀት ሰዎች እየመረጠ እና እየነጠለ ድል ያለ ድግስ በየሆቲሉ በመደገስ በውስኪና በጮማ ሲያንበሸብሻቸው መክረሙን የሰሙና ያዩ ሌሎች አባሎቹ በማኩረፍ የውሎ አበሎቻቸውን ከየአቅራቢያ ቀበሌዎች በመወሰድ ከድጋፍ ሰልፉ እራሳቸውን አግልለው ወደ የቤታቸው በመመለሳቸው በከፍተኛ ባለስልጣኑ ዘንድ ድንጋጤና ፍርሀት መፈጠሩን የደረሰን ጥቆማ ገልፆዋል::

በአዲስ አበባ የሚገኙት የወያኔ አዳዲስ እና ነባር አባሎች በሚደረግባቸው አድልኦ የተነሳ ሁልጊዜ አንገታቸውን ደፍተው ከማለፍ በስተቀር መናገር አለመቻላቸውን ተከትሎ የግንቦት 20ን በዓል ምክንያት ተደርጎ ቁልፍ ቁልፍ የተባሉ የብአዴንና የህወሀት ነባር ታጋዮች ብቻ እየተመረጡ በየድግሱ ላይ እንዲገኙና በግበዣ እንዲምበሸበሹ ከመደረጉም በላይ የተለያዩ የተስፋ ቃሎች በምስጢር እየተገባላቸው መሆኑን የተገነዘቡት አዳዲስ እና ወጣት አባሎች ማኩረፍ በመጀመራቸው በዕለቱም አደባባይ ባለመገኘት ተቃውሞዋቸውን ማሳየታቸውን ተከትሎ በወያኔ ውስጥ ፍርሀት መንገሱ ታውቆዋል::

ፍርሀትና ጭንቀት የገባው የወያኔ ዘረኛ ቡድን ችግሩን በአጭሩ ለመቅጨት ሲል በየመስሪያ ቤቱ በበዓሉ ላይ የተገኙና ያልተገኙ በሚል ስም ዝርዝራቸው ተለቅሞ ለማስፈራራት ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ መለጠፍ የጀመረ ከመሆኑም በተጨማሪ በቅርቡ የማጥሪያ ግምገማ እንዲደረግ እቅድ ማውጣቱንም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

የመስቀል አደባባይን በሰው ብዛት ጨረቃ እናደርገዋለን ብለው የወያኔ ካድሬዎች እየዛቱና በየሰፈሩ ቤት ለቤት ቅስቀሳ ከማድረግ አልፈው በግዳጅ እንገኛለን ብላችሁ ፈርሙ ተብሎ ህዝቡን ቢያስፈርሙም ወያኔዎች ያሰቡትን ያህል ቁጥር ቀርቶ አባሎቹ የሚላቸው ጭምር ሳይገኙ በመቅረቱ ስብሰባው በ10 ደቂቃ ንግግር ሊቋዋጭ ችሎዋል::

ብዙዎቹ አባሎች የወያኔ ነባር ታጋዮች በሚፈፅሙት ድርጊት ፍጹም ደስተኛ እንዳልሆኑ እና በውስጣቸው ይፋ አድልኦ በመስፈኑ እየተበሳጩ ከቀን ወደ ቀን ወያኔን በየአደባባዩና በየመሽታ ቤቱ እያወገዙት ሲሆን በተለይ ወጣት እና ከዩኒቨርስቲ የወጡትና በየመስተዳደር ውስጥ የተመደቡት ጭምር የወያኔን ዝርክርክና ዘረኛ አካሄድ እየተቹ እንደሚገኝም የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

የግንቦት 20 በዓልን በድምቀትና በደስታ ያላከበረው የወያኔ ቡድን መሪ መለስ ዜናዊ በድጋሚ የግንቦት 20 መዝጊያ በዓል በሚል በሚሊኒየም አዳራሽ ውስጥ በተዘጋጀ ድግስ ላይ ወጣትና ሴቶች ሊግ አባሎች እንዲገኙ ተጋብዘው የነበረ ቢሆንም እዛም ጥቂት ሰዎች ብቻ በመገኘታቸውና የተጠበቀውን ያህል ሳይገኝ በመቅረቱ የተበሳጨው መለስ በማግስቱ የከተማ ፕላን ውይይት በሚል በአስቸኳዋይ የክልል ባለስልጣናት ጭምር በጠቅላይ ሚኒስትር መሰብሰቢያ አዳራሽ እንዲገኙ ተደርጎ ለሶስት ቀናት ግምገማና ውይይት እንዲያደርጉ መገደዳቸው ታውቆዋል::

አንዳንድ ባለስልጣናትን በመጠራጠር የግዳጅ እረፍት እንዲያደርጉና በቅርብ ርቀት ላይ በደህንነት እንዲጠበቁ እየተደረገ ሁኔታቸው ተጠንቶ እንደገና ወደ ስልጣን እንደሚመለሱ የጠቆመው የደረሰን ዘገባ ግንባር ቀደም ተጠቂና የ15 ቀን የቁም እስረኛ ሆኖ የሰነበተው የደቡብ ክልል ፕሬዝዳንት ሽፈራው ሽጉጤ አንዱ እንደሆነ ዘገባው አብራርቶዋል::

ሌላው የጅንአድ ስራ አስኪያጅ የነበረውና የወያኔ አባሉ በየጊዜው ነባር ታጋይ ነን የሚሉትን በመቃወምና በመተቸቱ የተነሳ ያሰጋል ከሚባሉት ውስጥ አንዱ በመሆኑ ከኃላፊነቱ እንዲነሳ መደረጉንም የደረሰን ዘገባ ጨምሮ ያስረዳል::

አቶ ይማም መሐመድ የተባለው ለረጅም ዘመን በስራ አስኪያጅነት ሲሰራ የነበረው ግለሰብ ወያኔ የጣለውን የዋጋ ተመን በቂ ጥናት የተደረገበት ስላልሆነ ብዙ አያራምድም በሚል ሲቃወም የነበረ በመሆኑና ባለስልጣናቱ ከጅንአድ በዘመዶቻቸው ስም በሚወስዱት እቃ ዙሪያ ጠንካራ ተቃውሞ በማቅረቡ ምክንያት ከቦታው እንዲነሳና ለቁጥጥር እንዲያመች በዚያው አቅራቢያ አማካሪ ሆኖ እንዲቀጥል መደረጉን ዘገባው አብራርቶዋል::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የራሴ ናቸው የሚላቸውን ጭምር በመጠራጠር እያሰረና እያንገላታ ሲሆን የወጣት እና የሴቶች ሊግ አባሎችን ደግሞ እየተለማመጠ ቀጣይ ስልጣን የምትረከቡት እናንተ ብቻ ናችሁ እያለ ቅሰቀሳ መጀመሩም የጭንቀቱ ማሳያ ነው ተብሎዋል::

ባለፈው ሳምንት ውስጥ ሁለት ግዜ አንዱን በሚሊኒየም አዳራሽ አንዱን ደግሞ በስድስት ኪሎ የስብሰባ ማዕከል ጠርቶ ሲማጸናቸው የከረመው መለስ ዜናዊ እንደወትሮው ባለስልጣናቱን አስከትሎ መሄድ ትቶ ብቻውን እየገባ መማጸኑም የፍርሀቱ መጠን እየጨመረ መሆኑንም ነው እየተገለፀ ያለው::

የወያኔ ጉዞና አላማ የገባቸው አንዳንድ ወጣት አባሎችም በየጊዜው ቡድኑን እየለቀቁ ወደ የግል ድርጅት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ እየገቡ ሲሆን ሌሎችም ባሉበት ሆነው እየተቹት እና ውስጥ ውስጡን እየተቃወሙት እንደሚገኙ ታውቆዋል::

በመጨረሻም መላ የሀገሪቱ ህዝብ መብራት በፈረቃ እየተዳረሰ አንዳንዴም ከነጭራሹ እስከ 15 ቀናት ተከታታይ እየጠፋ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እየከረመ ባለበት በአሁኑ ወቅት ለጅቡቲ ተሸጦ ስራ መጀመሩ ታወቀ::

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ውስጥ አዋቂ ምንጮች እንደገለፁት ከሆነ ከያዝነው ወር ግንቦት አጋማሽ ጀምሮ ለጅቡቲ በቀን 25 ሜጋ ዋት መሸጥ የተጀመረ ሲሆን ይህንኑ ተከትሎ ከወትሮው በበለጠ በሀገሪቱ ውስጥ የመብራት ችግር እንደተፈጠረም ከተለያዩ ከተሞች የሚደርሱን ጥቆማዎች ያስረዳሉ፡፡

የመስመር ዝርጋታውንና የታወር ተከላውን ለማካሄድ ብቻ ከግማሽ ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ ገንዘቡን ከአፍሪካ ልማት ባንክና ከሌሎችም አለም አቀፍ ተቋዋሞች በብድር የተገኘና አብዛኛውን የመብራት ኃይል መሀንዲሶችና ባለሙያዎች የተሳተፉበት እንደነበርም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

ዛሬ በመላ ሀገሪቱ የመብራት ችግር ስር ሰድዶ ባለበት በዚህ ግዜ ከሀገር ውስጥ ይልቅ ለባዕዳን እያጎበደደ ያለው ወያኔ አሁንም ህዝቡን ለችግር እና ለድቅድቅ ጨለማ ከትቶ ለባዕዳን መሸጡ አስገራሚ ነው ሲሉም እነዚሁ የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ትዝብታቸውን ይገልጻሉ፡፡